INTERME

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ማ/ቅ/ጽ/ቤት
EHTIOPIAN REVENUE AND CUSTOMS
AUTHORITY
A.A. KAIITY CUSTOMS BRANCH OFFICE

የውስጥመጻጻፊ

ቁጥር: ም/ሥ/ጉ/ጉ/00334/10
ቀን: 18/07/2010

- ለጉምሩክ ስነ ስርዓት አፈፃፀም የስራ ሂደት
- ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት
- ለደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ሂደት
- ለመጋዘን አስተዳደርና ቁጥጥር የሥራ ሂደት
- ለሀብት አስተዳደር ስራ ሂደት
- ለቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጉ/ስ/ስ/አ/ስራ ሂደት
- ለኢስተርን ኢንዱስትሪ ዞን ጉ/ስ/ስ/አ/ስራ ሂደት
- ለገላን ተርሚናል ጉምሩክ ማስተባበሪያሽ
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት

- ከ: ጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ
  አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

የዋና መ/ቤት የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሰራር ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በቁጥር 4.3/101/10 መጋቢት 12/2010 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ በቀን 12/06/2010 በቁጥር መኢ.ቴሚ/ስታ/1074/2010 በቴሌኮሚኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 አንቀጽ 14/4 በተደረገው መሰረት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸውን የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች የመገናኛ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሳይፈቀድ ማምረት ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ማከፋፈል የተከለከለ መሆኑን የገለፀ መሆኑንና ሚ/ር መ/ቤቱ ባስተላለፈው ደብዳቤ መሰረት ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው መሳሪያዎች ዝርዝር መሰረት ወደ አገር ሲገቡ ከመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ፍቃድ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ያሳወቁን ስለሆነ ለአፈፃፀም ይረዳችሁ ዘንድ የተላከውን 4 ገጽ ደብዳቤ በአባሪነት አያይዘን ልከንላችኋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣
- ለሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
- ለም/ስራ አስኪያጅ /ህግ ማስከበር ዘርፍ/
  አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 4.3/201/10
Ref. No
ቀን 04 መጋቢት 2010
Date

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈጸምባቸዉ ቅ/ጽ/ቤቶች

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>ከዉጭ ወደ ሀገር ዉስጥ የሚገቡ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸዉ መሳሪያዎች ዝርዝር መላክን ይመለከታል፡፡</u>

በቀን 12/06/2010 በቁጥር መኢቴሚ/ስታ/1074/2010 በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 አንቀጽ 14/4 በተደነገገዉ መሰረት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸዉን የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በቅድሚያ ሳይፈቅድ ማምረት ፣ወደ ሀገር ዉስጥ ማስገባት ወይም ማከፋፈል የተከለከለ መሆኑን ገልጾ አሳዉቋል፡፡

በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባስተላለፈዉ ደብዳቤ መሰረት ከዉጭ ወደ ሀገር ዉስጥ የሚገቡ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸዉ መሳሪያዎች ዝርዝር መሰረት ወደ አገር ሲገቡ ከመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ፈቃድ የሚያስፈልጋቸዉ ስለሆነ አስፈላጊዉ እንዲፈጸም እያሳወቅን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላለፈዉን ዉሳኔ የሚገልጽ 03 ገጽ ኮፒ አባሪ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ጌቱ ለገሠ
የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሰራር ድጋፍ_ዳይሬክቶሬት

<u>ግልባጭ</u>

- ለክቡር ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለህግ ማስከበር ዘርፍ
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሰራር ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤቶች
- ለታሪፍ ምደባ አሰራር ድጋፍ ቡድን

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

662
10/07/2010

12/10
-07-10

ጉ/አ/1039
07/07/10

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Communication & Information Technology

ቁጥር
Ref.No. መኢቴሚ/አተ/1041

ቀን
Date. 12/06/2010

ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው መሣሪያዎች ዝርዝር መላክን ይመለከታል፤</u>

በቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር 49/1989 አንቀጽ 14(4) በተደነገገው መሠረት የሚኒስቴሩ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸውን የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ሚኒስቴሩ በቅድሚያ ሳይፈቅድ ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ማከፋፈል የተከለከለ ነው፡፡

በተጨማሪም በቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል አዋጅ ቁጥር 761/2004 አንቀጽ 3(1) በተደነገገው መሠረት ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጭ ማንኛውም የቴሌኮም መሣሪያ የሚያመርት፣ የሚገጣጥም፣ ከውጭ ሀገር የሚያስመጣ ወይም የሚሸጥ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 100,000.00 እስከ ብር 150,000.00 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 3(2) በተቀመጠው መሠረት ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጭ ማንኛውም የቴሌኮም መሣሪያ የሚጠቀም ወይም ይዞ የሚገኝ ማንኛውም ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከ1 እስከ 4 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 10,000.00 እስከ ብር 40,000.00 በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

በዚሁ መሠረት የአዋጆቹን ድንጋጌዎች ሥራ ላይ ለማዋል የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በአዲስ አበባ ኤርፖርት የካርጎ ተርሚናል ከውጭ ሀገር ለሚገቡ መሣሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ እና ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩ መሣሪያዎችን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳይፈቅድ ማምረት፣ መገጣጠም፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ማከፋፈል፤ መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት ክልክል መሆኑ ታውቆ መሣሪያዎቹ በመንገደኞች፣ በካርጎ እና በደረቅ የወደብ አገልግሎት ጣቢያዎች ሲደርሱ በሚኒስቴር

1028 ☎ +251-11-552-1381 ፋክስ Fax +251-11-554-7475 ኢ-ሜይል/e-mail mcit@mcit.gov.et

መ/ቤቱ ተረጋግጠው የመግቢያ ፈቃድ ሳይሰጥባቸው ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ተገቢው ጥብቃቂ እንዲደረግ እንጠይቃለን፡፡

| ተ.ቁ | የመሣሪው አይነት | Type of Equipment |
|---|---|---|
| 1 | ባለገመድ መደበኛ ስልክ (መደበኛ እና የአለቃና ጸሀፊ ስልክ) | Corded Telephone Handset (Ordinary, Executive, secretarial sets) |
| 2 | ገመድ አልባ መደበኛ ስልክ | Cordless Telephone handsets |
| 3 | የኢንተርኔት ፕሮቶኮል /IP/ ስልክ | IP Phones |
| 4 | የሲዲኤምኤ መደበኛ ገመድ አልባ ስልክ | CDMA Wireless Telephone Handsets |
| 5 | የጂኤስኤም 2G/3G/4G እና ሲዲኤምኤ ሞባይል ስልክ | GSM 2G/3G/4G and CDMA Mobile Phones |
| 6 | የሳተላይት ሞባይል ስልክ | Satellite Mobile Phones |
| 7 | ኤዲኤስኤል ሞደም | ADSL Modems |
| 8 | ሲም ካርድ የሚወስዱ አይፓድ፣ ታብሌት እና ኖትቡክ | iPAD, Tablet and notbooks with SIM card Functionalities |
| 9 | የፋክስ ማሽን | Fax machines (Facsimile Transcievers) |
| 10 | የግል ቅርንጫፍ ማዞሪያ (ፒቢኤክስ) | Call Routing Devices (Private Branch Exchange (PBX). Key Telephone System (KTS), Small Business System (SBS) |
| 11 | **የኔትወርክ መሣሪያዎች** | **Network Devices** |
| 11.1 | ሞደም | Modem |
| 11.2 | ስዊች | Switch |
| 11.3 | የመገናኛ ሰርቨር | Communication Server |
| 11.4 | ራውተር | Router |
| 12 | **የአጭር ርቀት መሣሪያዎች** | **Short Range Devices (SRDs)** |
| 12.1 | የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ መለያ መሣሪያዎች | Radio Frequency Identifier Devices (RFID) |
| 12.2 | የቴሌሜትሪ ሞጁሎች | Telemetry and Command Modules |
| 12.3 | ገመድአልባ ማይክሮፎኖች | Wireless Microphones |
| 12.4 | የመኪና በር መክፈቻ እና አላርም መሣሪያዎች | Remote Keyless Entries and Access Control Devices |
| 12.5 | ገመድ አልባ የአላርም መሳሪያዎች | Wireless Alarm Systems |
| 12.6 | ገመድ አልባ የሎካል ኤሪያ ኔትወርክ ካርዶች | Wireless LAN cards |
| 12.7 | ገመድ አልባ የዋይፋይ መሣሪያዎች | Wireless Access Point (WAP) Devices |
| 13 | ኤችኤፍ ፣ ቪኤችኤፍ እና ዩኤችኤፍ የመገናኛ ሬዲዮ | HF, VHF, and UHF Communication Radios |

Ethiopian Revenues & Customs Authority

| ተ.ቁ | የመሣሪው አይነት | Type of Equipment |
|---|---|---|
| 14 | አማተር የመገናኛ ሬዲዮ | Amateur Communication Radios |
| 15 | የቴሌቪዥን ስርጭት ብቻ መቀበያ ሬሲቨር | Television Receive Only (TVRO) Receivers |
| 16 | ኢልኤንቢ | LNB |
| 17 | ቪኤችኤፍ እና ዩኤችኤፍ የመገናኛ ሬዲዮ ሞደም | VHF and UHF Communication radio Modems |
| 18 | የሬዲዮ ሞደም የተገጠመበት ጂፒኤስ | GPS with installed communication Radio Modems |
| 19 | የማሰራጫ እና መቀበያ አንቴናዎች | Transmission and Receiver Antennas |
| 20 | **የቪሳት መሳሪያዎች እና መለዋወጫዎች** | **VSAT Equipment and Accessories** |
| 20.1 | የቪሳት አንቴና/ዲሽ | VSAT Antenna/Dish |
| 20.2 | ብሎክ አፕ ኮንቨርተር | Block UP-Converter (BUC) |
| 20.3 | ሎው ኖይዝ አምፕሊፋየር | Low noise Amplifier (LNA) |
| 20.4 | ሃይ ፓወር አምፕሊፋየር | High Power Amplifier |
| 20.5 | ሳተላይት ሞደም/ራውተር | Satellite Modem/Routers |
| 21 | የኢቪዲኦ፣ ሲዲኤምኤ እና የሞባይል ዶንግሎች፣ ዩኤስቢ ሞደሞች እና የዳታ ካርዶች | EVDO, CDMA and Mobile Dongles, USB Modems and Data Cards |
| 22 | በሲም ካርድ የሚሠሩ የእንቅስቃሴ መከታተያ መሣሪያዎች | Tracking Devices with SIM card functionalities |
| 23 | የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ማዞሪያ እና ማስተላለፊያ መሣሪያዎች | Telecommunication Network Exchange and Transmission Equipment |

በተጨማሪም ከቴክኖሎጂው ተለዋዋጭነት እና ዕድገት አኳያ በማየት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈቃድ የሚስፈልጋቸውን ሌሎች ከቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተልማቱ ጋር የሚገናኙ የቴሌኮሙኒኬሽን እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን ዝርዝር በየወቅቱ በማሻሻል የሚያሳውቅ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፣

ለኢትዮጵያ ገቢ[illegible] ባለስልጣን

አዲስ አበባ

Ethiopian Revenues & Customs Authority
Records & Documentation No.2